ይሆን ፡ መልእክቴን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ በጎ ፡ አድራጎትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ እምነት ፡ እንዳይለየኝ ፡ ተስፋ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈቀድልኝ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የግርማዊ ፡ የሄሌኖች ፡ ንጉሥ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤዎን ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

በሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የቆየው ፡ ጽኑ ፡ ወዳጅነት ፡ ሊጋራ ፡ አሳባችንና ፡ ጥቅማችን ፡ መሠረት ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ግንኙነት ፡ እጅግ ፡ እያቀራረበ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ፖል ፡ ያደረጉልንን ፡ ጥሪ ፡ ተቀብለን ፡ ታላቅ ፡ አገራቸውን ፡ ለመጐብኘት ፡ በመቻላችን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህም ፡ ያደረግነው ፡ መጐብኘት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነትና ፡ መተሳሰብ ፡ እያጠነከረ ፡ የሚሄድ ፡ ለመሆኑ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። በዚያች ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፤ የግሪክ ፡ ሕዝብና ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ላደረጉልን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አቀባበል ፡ ለሕዝቡና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የነበረን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ ተገልጸዋል ።

በሄድንበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡ ፡ በገለጸልን ፡ የደስታ ፡ ስሜትና ፡ ባደረገልን ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ልባችን ፡ በጥልቅ ፡ ተነክቷል ። በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ሊያለውን ፡ ወዳጅነት ፡ የበለጠ ፡ ለማጠንከርና ፡ ለማስፋፋት ፡ ያለብዎን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መልክት ፡ ለመፈጸም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ እርዳታችን ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ሊተማመኑ ፡ ይችላሉ ።

ክቡርነትዎ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ፖል ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታችንን ፡ እንዲያቀርቡልንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፤ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ ለግሪክ ፡ ሕዝብ ፡ ደኅንነትና ፡ ደስታ ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

468

ለኤሌክትሪክና ፡ ለራዲዮ ፡ ሜካኒክ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ የሚሄዱ ፡ ፮ ፡ ወጣቶች ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፯፻፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ወጣቶቹ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡

ሀ) ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ።

የኢትዮጵያ ፡ ብርሃን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በዚህኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የምንገኝ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ አባት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለ ፡ ስጠን ፤ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ ዓለም ፡ ከደረሰበት ፡ ደረጃ ፡ እንድንደርስ ፡ የተከፈተልን ፡ የዕውቀት ፡ ጥቂያ ፡ ከእኛም ፡ አልፎ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድን ፡ የሚያኰራ ፡ ታላቅ ፡ የታሪክ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብታም ፡ የሆነችው ፡ ሀገራችን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ፡ በሚያፈልቀው ፡ ቴክኒካዊ ፡ ጥበብ ፡ እንድትጠቀምና ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ እንድትራመድ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ በብዛት ፡ በማቋቋምዎ ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ ገና ፡ ባልጋ ፡ ወራሽነት ፤ ቀጥሎም ፡ ታላቁን ፡ አደራ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ከፍተኛውን ፡ አስተያየትዎን ፡ በተለይ ፡ ያሳረፉት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ በማቋቋምና ፡ የወጣቶችን ፡ አእምሮ ፡ በዕውቀት ፡ በማጐልመስ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍሬ ፡ እየሰጠ ፡ በመሄዱ ፡ ድካምዎ ፡ የተባረከ ፡ ሆኗል ።

ይህም ፡ ሕዝብዎ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የመላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆቱን ፡ አስፍሮበታል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከሚገኙት ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ ከሚቈጠሩት ፡ ወጣቶች ፡ በቀር ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የተለመደ ፡ ልግሥናና ፡ ያባትነት ፡ አስተያየት ፡ ብዙዎች ፡ ተማሪዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገሮች ፡ ተልከው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበቦች ፡ በመቅሠም ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

እኛም ፡ በግርማዊትዎ ፡ አባትነት ፡ በተግባረ ፡ እድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተማርን ፡ አራት ፡ ወጣቶች ፡ ይኸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ደርሶን ፡ የራዲዮና ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ከፍተኛ ፡ ቴክኒካዊ ፡ ጥበብ ፡ ለመማር ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ልንሄድ ፡ ስለ ፡ ተዘጋጀን ፡ ዛሬ ፡ ከገናናው ፡ ዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ ስንሰናበት ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ደስታ ፡ ይሰማል ።

ግርማዊነትዎ ፡ በየጊዜው ፡ ለወጣቶች፡ የሚሰጡትን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የአባትነት ፡ ምክር ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በትጋት ፡ ቀጥለን፡ ከፍጻሜ ፡ ካደረስን ፡ በኋላ ፡ እናት ፡ አገራችንንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ባፈራ ነው ፡ ዕውቀት ፡ ለማገልገል ፡ ያለን ፡ ምኞት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ስን ገልጽ ፡ ለዚህ ፡ ዕድል ፡ ላበቃን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ልባዊ ፡ ምስጋና ፡ እና ቀርባለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ፦

የምትላኩበት ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ተገነዘባችሁት ፡ ሁኔታውን ፡ ዘርዝራችሁ ፡ ገልጣችሁልናል ። የተናገራችሁትን ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የምትችሉት ፡ ከልጅ ፡ ጠባይ ፡ ርቃችሁ ፡ ሙሉ ፡ አስተያየታ ችሁን ፡ በትምህርታችሁ ፡ ላይ ፡ ስታውሉት ፡ ነው ።

በሀገሩ ፡ ላይ ፡ በደረሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውንም ፡ በዐይናችሁ ፡ በማ የት ፡ ትረዱታላችሁ ። አሁን ፡ የምናሳስባችሁ ፡ የመምህራኑን ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቃችሁ ፡ የሚያስተምሯችሁን ፡ ትምህርት ፡ በትጋት ፡ እን ድትከታተሉ ፡ ነው ።

በውጭ ፡ አገር ፡ በምትቈዩበት ፡ ጊዜ ፡ ከማናቸውም ፡ መጥፎ ፡ ተግ ባር ፡ ብትርቁ ፡ ራሳችሁን ፡ አስከበራችሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ንኑ ፡ ተገንዝባችሁና ፡ ትምህርታችሁንም ፡ በትጋት ፡ ቀጥላችሁ ፡ ራሳች ሁንና ፡ አገራችሁን ፡ ለመርዳት ፡ እንድትበቁ ፡ እንመኝላችኋለን ።

469

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሥተው ፡ ሆለታ ፡ ፴፬ተኛው ፡ ኪሎ ፡ ሜትር፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተገኝተው ፡ የ፲፩ኛውን ፡ ኮርስ ፡ ፈተና ፡ ላለፉ ፡ ፷፩ ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሰጡ ። እጩ ፡ መኰንኖቹም ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ አስተማሪያቸው ፡ በአቶ ፡ አባተ ፡ መንግሥቱ፡ አማካይነት ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ጠያቂና ፡ ተጠያቂ ፡ በመሆን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ አጸጸፋና ፡ ንግግር ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ አሳዩ ።

የአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ፕሮግራም ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ከ፴፭ ፡ ደቂቃ ፡ ተፈጸመና ፡ ከሆለታ ፡ ፲፯ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቆ ፡ በሚገኝ ፡ በበርጋ ፡ አቅራቢያ ፡ ቱሉ ፡ ኮርማ ፡ በሚባል ፡ ቀበሌ ፡ በአጥቂና ፡ በተጠቂ ፡ ጦር ፡ የተዘጋጀውን ፡ የጦር ፡ ታክቲክ ፡ የመለማመጃ ፡ ውጊያ ፡ ለመመልከት ፡ በአንድ ፡ ልዓላዊ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።

በመድፍና ፡ በከባድ ፡ አዳፍኔ ፡ በከባድና ፡ በቀላል ፡ ታንክ ፡ የተደረገውን ፡ የውጊያ ፡ ልም ምድ ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ በዚያው ፡ ቀበሌ ፡ በተዘጋጀው ፡ ስፍራ ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ ሆነ ። ከግብዣው ፡ በኋላ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በ፷፩ ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ መካ ከል ፡ በተገኙበት ፡ ላይ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አዛዥ ፡ ሌ/ ኰሎኔል ፡ ይልማ ፡ ሺበሺ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ሀ) የሌ/ ኰሎኔል ፡ ይልማ ፡ ሺበሺ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ይህ ፡ ውድድር ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፤ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ የበታች ፡ ሹማምንቶች ፡ ውስጥ ፤ ፫፪ ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ ውድድር ፡ እንዲቀጥል ፡ በተፈቀደው ፡ መሠረት ፡ ከሻለቃ ፡ እስከ ፡ ብርጌድ ፡ ከብርጌድ ፡ እስከ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ባለ ፡ ሌላ ፡ ማዕርጎች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ፈተና ፡ ተደርጎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ፲፱፻፷ ፡ ባለ ፡ ሌላ ፡ ማዕ ረጎች ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ፈተና ፡ በማለፍ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ወጊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጥተው ፡ ለ፫ ፡ ወር ፡ የምርጫ ፡ ውድድር ፡ ተደ ርጎ ፡ ከ፲፱፻፷ ፡ የበታች ፡ ሹሞች ፡ ውስጥ ፡ ፹፯ቱ ፡ የምርጫ ፡ ፈተናቸውን ፡ አልፈው ፡ ትምህርታቸውን ፡ በመቀጠል ፡ የዛሬውን ፡ ዕድል ፡ ለማግኘት ፡ ከተሰለፉት ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ውድድሩን ፡ እንዳጋመሰ ፡ ታሞ ፡ በሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲለይ ፡ የቀሩት ፡ እነሆ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርበዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ።

እነዚህ ፡ ዛሬ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ለመቅረብ ፡ ዕድል ፡ ያገኙት ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ተመልሰው ፡ ዘመናዊውን ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በአቋቋሙ ፡ ጊዜ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ የሻለቃ ፡ ባሻዎች ፡ በስተቀር ፡ በየክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የልጅ ፡ ወታደሮች ፡ እንዲቋቋም ፡ በታቀደው ፡ መሠረት ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ከ፲ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ልጆች ፡ እያሳደገ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የመንፈስ ፡ አባትነት ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሞግዚትነት ፡ ወላጆቻቸው ፡ በምንም ፡ ረገድ ፡ ሳይቸገሩ ፡ ለ፴ ፡ ዓመት ፡ የአማርኛና ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትምህርት ፡ ሒሳብ ፡ በማስጠናት ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃን ፡ ትምህርት ፡ አልፈው ፡ እንደገናም ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ውድድር ፡ ጨርሰው ፡ በየጦሩ ፡ ውስጥ ፡ ተደልድለው ፡ በወታደር ፡ አመራር ፡ ሲያገለግሉ ፡ የቆዩ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ልጆች ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ አስቀድሜ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ ሁሉ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ረድኤት ፡ አድገው ፡ ለዚህ ፡ የደረሱ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ የማላፍርበት ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ።

ለዚህ ፡ ዓይነት ፡ ውድድር ፡ መደብ ፡ የሚገባው ፡ የትምህርት ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ቢሆን ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ የቆዩና ፡ በአብዛኛውም ፡ የወታደር ፡ ትምህርት ፡ አስቀድሞ ፡ የሠለጠኑ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያሁኑ ፡ ውድድር ፡ የማታ ፡ ትምህርትን ፡ ጨምሮ ፡ እንዲሠራ ፡ ተደርጎ ፡ ዛሬ ፡ በዘጠኝ ፡ ወሩ ፡ ተፈጽሟል ።

እጩ ፡ መኰንኖችም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የመኰንን ፡ ማዕርግ ፡ ለማግኘት ፡ ያደረጉት ፡ ጥናትና ፡ የሥራ ፡ ትጋት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውጤት ፡ አስገኝቷል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ።

እነዚህም ፡ ዛሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ተመርቀው ፡ የሚወጡት ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡

* * *

አዲስ ፡ ሳይሆኑ ፡ ነባር ፡ አባሎች ፡ በመሆናቸው ፡ ታማኝነታቸውን ፡ እያደሱ ፡ እንደሚያገለግሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

* * *

ለ) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

በትምህርት ፡ ጕልምሳችሁ ፡ ስናያችሁ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለናል ። ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ በመካከላችሁ ፡ ተገኝተን ፡ ከተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ በአንዱ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ አሳባችሁን ፡ ስትገላለጡ ፡ በመስማታችን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶናል ። ቋንቋ ፡ ማወቅ ፡ በሀገራችን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ለክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠቃሚና ፡ ምስክር ፡ የሆኑትን ፡ መጻሕፍት ፡ ለማግኘት ፡ የቻልነው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የነበሩት ፡ አባቶቻችን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየሄዱ ፡ በርትተውና ፡ ተግተው ፡ በመማራቸውና ፡ ከቋንቋ ፡ ወደ ፡ ቋንቋ ፡ ከመተርጐማቸው ፡ የተነሣ ፡ ነው ። በኋላ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እየተቋረጠና ፡ እየጠበበ ፡ ሄደ ። ምክንያቱንም ፡ ታውቁታላችሁ ፤ መከፋፈልም ፡ የመጣው ፡ ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ነው ።

ቀደም ፡ ብላችሁ ፡ ስትናገሩ ፡ እንደሰማነው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሁለተኛ ፡ ቋንቋ ፡ መሆኑን ፡ አስታውሳችኋል ። ስለዚህ ፡ ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ በማጥቃት ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባለመታደል ፡ መማረክም ፡ ስለሚኖር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቋንቋ ፡ የሚያገለግል ፡ የበለጠ ፡ መሣሪያና ፡ ኃይል ፡ ይሆናል ። ከብዙ ፡ ትምህርት ፡ አንዱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ማወቅ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸንላችኋል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ ፡ ማወቅ ፡ አይበቃም ። የሀገርንም ፡ ቋንቋ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ይጠቅማል ።

ኢትዮጵያዊ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ አማርኛ ፡ አለማወቅ ፡ አገር ፡ የለኝም ፡ እናት ፡ አባቴንም ፡ አላውቅም ፡ የማለት ፡ ያህል ፡ አሳፋሪ ፡ ነገር ፡ ነው ። አስቀድሞ ፡ ያገርን ፡ ቋንቋ ፡ አጥርቶ ፡ ማወቅ ፤ ቢቻልም ፡ ግዕዝን ፡ ጨምሮ ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቁትን ፡ ወጣቶች ፡ መምረጣችንን ፡ ታውቃላችሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ እንደዚሁ ፡ በብርታት ፡ ተምራችሁ ፡ ስናያችሁ ፡ ደስ ፡ ይለናል ። አባቶቻችሁንም ፡ ያስመሰግናል ። ከዚያም ፡ በቀር ፡ በአዋጅ ፡ ልጁን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ የማይረዳ ፡ ያገር ፡ ደመኛ ፡ ነው ፡ ያል

ነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ወንድነትም ፡ ከትምህርት ፡ ይገኛል ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ታሪክን ፡ ያነባል ። ታሪክ ፡ የሚገኘው ፡ ከጅግንነት ፡ ነው ። ጅግናን ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰዋል ። ይሉኝታን ፡ ያስከትልለታል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎችን ፡ ማወቅና ፡ የጠለቀ ፡ ትምህርት ፡ ማግኘት ፡ አሚሚትን ፡ ያሳምራል ። ወደ ፡ ክብር ፡ ደረጃም ፡ ያደርሳል ። ውለታ ፡ ቢስ ፡ ከመሆን ፡ ያድናል ። የዲስፕሊንን ፡ ጣዕም ፡ ለማወቅ ፡ ያስችላል ። በመጨረሻም ፡ ወደምንሄድበት ፡ ተስፋ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪያችን ፡ መቅረቢያው ፡ መሰላል ፡ ትምህርትን ፡ ማወቅና ፡ መመራመር ፡ ነው ።

ፈሪነት ፡ የማይድንን ፡ ስም ፡ ለዘሩ ፡ አስትቶ ፡ ከማለፉ ፡ በላይ ፡ ለራሱም ፡ መጥፎ ፡ ባለ ፡ ታሪክ ፡ እንደማይድን ፡ ቁምጥናና ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ የሚያስቆጥረው ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ ባሳያችሁንና ፡ በተመለከትነው ፡ እርምጃ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። አስተማሪ ፡ በማምጣታችን ፡ ስለአገራችን ፡ ጉዳይ ፡ ለሠራናቸው ፡ ፕላኖች ፡ ተስፋችንን ፡ ያበረታል ። ይህ ፡ የሰጠናችሁ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ያሁን ፡ ደስታ ፡ መስሎ ፡ ቢታያችሁ ፡ ሳትሠሩበት ፡ ቀርታችሁ ፡ የኋላ ፡ በሽታ ፡ እንዳይሆንባችሁ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለባችሁ ።

ይህ ፡ የሰጠናችሁ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ብትሠሩበት ፡ በእድገት ፡ ላይ ፡ እድገት ፡ የሚጨምርላችሁ ፡ ነው ። ያሁኑን ፡ ደስታ ፡ አትመልከቱ ። በሙሉ ፡ ልባችሁ ፡ የገባችሁበትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በቅንነትና ፡ በትጋት ፡ በታማኝነት ፡ አገራችሁንና ፡ እኛን ፡ አገልግላችሁ ፡ ብትገኙ ፤ ይህ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚመሰክርላችሁ ፡ ይሆናል ። ይህን ፡ ሳታደርጉ ፡ ብትቀሩ ፡ ግን ፡ የሚመሰክርባችሁ ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጉ ። ዘወትር ፡ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ መጣጣር ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባራችሁ ፡ ይሁን ።

ለማስተማር ፡ የተጉትንና ፡ የረዱትን ፡ መኰንኖች ፡ እናመሰግናለን። በተለይም ፡ አንተን ፡ እናመሰግንሃለን ።

470

የቤልጅክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ፒየር ፡ ሮየርሽ ፡ ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፯፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡

የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊ ፡ የቤልጅክ ፡ ንጉሥ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ የተሰጠኝን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤዬን ፡ ሳቀርብ ፡ ከሙሉ ፡ ልቤ ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነው ።

ከዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ለግል ፡ ጉዳዬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቼ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወራረስ ፡ የመጣውን ፡ የዚችን ፡ የሰፊና ፡ የተወዳጅ ፡ አገር ፡ ዝና ፡ አስቀድሜ ፡ አጥንቼዋለሁ ። ስለዚህ ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ በሥልጣኔ ፡ ከቀደሙት ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንድትገኝ ፡ የተወደዱ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በአፍሪካ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ የሚመራው ፡ ሥራ ፡ ብርሃን ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። በነበርኩበትም ፡ ጊዜ ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ባገናኘኝ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ ባደረጉልኝ ፡ የልብና ፡ የፍቅር ፡ አቀባበል ፡ ልቤ ፡ ተነክቷል ። በዚህም ፡ ባደረግነው ፡ ብዙ ፡ መቀራረብ ፡ ውስጥ ፡ ቤልጅክንና ፡ ኗሪ ፡ ሕዝቦቿን ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፡ ለማድረግ ፡ አስችሎኛል ። በዚህ ፡ በያዝናቸው ፡ ትውልዶች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለማዳን ፡ ሲሉ ፡ ተመሳሳይ ፡ ትግል ፡ አድርገዋል ። እነሱም ፡ በተወረሩ ፡ ጊዜ ፡ በብርታት ፡ ለመከላከላቸው ፡ የሚያጠራጥር ፡ አልነበረም ።

ይህን ፡ አዲሱን ፡ ሥራዬን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ቤልጅክን ፡ በበለጠ ፡ እየጠነከሩ ፡ በሚሄዱበት ፡ ተግባር ፡ በተቻለኝ ፡ ለመሥራት ፡ ከቶ ፡ ቸል ፡ እንዳልል ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ አደራ ፡ ብለውኛል ። እንዲሁም ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለሕዝቧ ፡ ልማት ፡ ያላቸውን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽ ፡ የተወደዱ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ የላኩኝን ፡ መልእክት ፡ ለመግለጽ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የግርማዊ ፡ የቤ ልጅኮች ፡ ንጉሥ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ በተሾሙበት ፡ በአዲሱ ፡ ሥራዎ ፡ በደስታ ፡ ስንቀበልዎ ፡ የተላኩበት ፡ ሥራ ፡ እንዲቃናልዎ ፡ ሁልጊዜ ፡ የምናስብበት ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ እንገልጽልዎታለን ። ሚኒስትሮቻች ንና ፡ ሕዝባችንም ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የኖረውን ፡ መልካም ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነትና ፡ የመገባባት ፡ ስሜት ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማጠንከር ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ እርዳታ ቸውን ፡ የሚያጓድሉበዎ ፡ መሆናቸውን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በኢትዮጵያ ፡ መኖርዎና ፡ ሕዝባችንንም ፡ ማወቅዎ ፡ የሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ግንኙነት ፡ ለማጠንከር ፡ በብዙ ፡ እንደሚረዳዎ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በግርማዊ ፡ የቤልጅኮች ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ገለጹዋቸው ፡ የሰላምታና ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ ቃሎች ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፡ ክቡርነትዎ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ቦድወን ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታችንን ፡ ለቤልጅክ ፡ ሕዝብ ፡ ልማትና ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

471

የሕንድ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሳርዳር ፡ ናራንጀን ፡ ሲናዳ ፡ ጀል ፡ ዋር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ በገነት ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ የአገሬ ፡ አም ባሳደር ፡ ለመሆን ፡ ተመርጬ ፡ ዛሬ ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤዬን ፡ ለግርማዊ

ነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ታላቅ ፡ ደስታና ፡ ኩራት ፡ ይሰማኛል ። ይኸንኑ ፡ ምክ ንያት ፡ በማድረግ ፡ የተከበሩ ፡ የሕንድ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬ ዚዳንት ፡ መንግሥታቸውና ፡ እሳቸው ፡ ያላቸውን ፡ ከፍተኛ ፡ ግምትና ፡ የጸና ፡ ወዳጅነት ፡ ልባዊ ፡ ሰላምታና ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለግርማዊነ ትዎ ፡ እንዳቀርብ ፡ አዘውኛል ።

ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ይልቁንም ፡ የሕንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሽሪ ፡ ጃዋሀርላል ፡ ኔህሩ ፡ እንደዚሁ ፡ በበኩላቸው ፡ ያላቸውን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንዳደርስ ፡ ባዘዙኝ ፡ መሠረት ፡ ይኸንኑ ፡ ለግ ርማዊነትዎ ፡ ለጀግናው ፡ ሕዝብዎና ፡ ለጥንታዊ ፡ አገርዎ ፡ ብልጽግናና ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ካለኝ ፡ ተስፋ ፡ ጭምር ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ አቀርባለሁ ። ከዚች ፡ ከጥንታዊት ፡ አገርዎ ፡ ጋር ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ በቀ ጥታ ፡ ግንኙነት ፡ ሊኖረኝ ፡ ዕድል ፡ ሳያጋጥመኝ ፡ ቢቀርም ፡ (ወይም ፡ ከቅ ርቡ ፡ ሳልመለከታት ፡ ብቀርም) ፡ ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ የፈጸመቻ ቸው ፡ የጀግንነት ፡ ታሪካዊ ፡ ሞያዎች ፡ በግርማዊነትዎ ፡ አስተዋይነት ፡ ብርቱ ፡ መሪነትና ፡ አነሣሽነት ፡ ነው ፡ ብል ፡ ይኸን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይ ስተውም ።

በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ብዙ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነገሮች ፡ ይገኛሉ ። የየራሳቸውን ፡ የጥንታዊ ፡ ጥበብና ፡ ሥልጣኔ ፡ የወ ረሱ ፡ ኩሩ ፡ አገሮች ፡ እንዲሁም ፡ ለሌሎች ፡ የዓለም ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ፈቃድን ፡ ሰላምንና ፡ ትዕግሥትን ፡ የሚመኙ ፡ ከመሆናቸ ውም ፡ በላይ ፡ ዛሬ ፡ በኤኮኖሚክና ፡ በሶሽያል ፡ (የማኅበራዊ ፡ አኗኗር ፡) ረገድ ፡ ለመጐልመስ ፡ ቊርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ያደረጉና ፡ የሚያስፈልጋቸውም ፡ ናቸው ።

በአገርዎ ፡ ውስጥ ፡ የአገሬ ፡ እንደራሴ ፡ አምባሳደር ፡ ለመሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ አግኝቼ ፡ በምቆይባቸው ፡ ዓመታት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሕን ድና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የቆ ዩት ፡ መልካም ፡ ግንኙነቶች ፡ እየተስፋፉ ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የምጥርበት ፡ ተግባሬ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ አሁን ፡ የያዝሁ ትን ፡ ሥራ ፡ ከፍጸሜ ፡ አድርሼ ፡ ስለቅ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በመካከላችን ፡ የነ በሩትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በማጠንከር ፡ የተሳካልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ድካሜ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ እንዳገኘ ፡ እቆጥረዋለሁ ።

ይኸንኑ ፡ ተስፋ ፡ በማድረግና ፡ በመጠበቅ ፡ ራሳቸው ፡ ቀርበው ፡ ለመስጠት ፡ ሳይመቻቸው ፡ የቀሩት ፡ ከኔ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የነበሩት ፡ አምባሳደር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤና ፡ ከሕንድ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሰጠኝን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ እጅ ፡ ስሰጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ የተቃረበ ፡ ወዳጅነት ፡ ላላት ፡ ለሕንድ ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስንቀበልዎ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ከእርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የተከበሩ ፡ አምባሳደር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ስንቀበል ፡ ስለርሳቸው ፡ የነበረን ፡ ግምት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑንና ፡ እርሳቸውም ፡ የወዳጃችን ፡ የታላቁ ፡ የሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ የተገቡ ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ መገኘታቸውን ፡ ልንገልጥ ፡ እንወዳለን ።

የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ የተመሠረተው ፡ ባላቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ ታሪክና ፡ ወግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተለየ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ ባደረጉት ፡ ተጋድሎና ፡ መሥዋዕትነት ፡ ላይ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለመመለስ ፡ በተደረገው ፡ ብርቱ ፡ ጦርነት ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉት ፡ የጀግናው ፡ የሕንድ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወታደሮች ፡ በኛም ፡ በሕዝባችንም ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አይረሱም ።

ከነዚያ ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመባቸው ፡ ቀኖች ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሕንድ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጎብረትና ፡ መረዳዳት ፡ ከልብ ፡ የመሆኑና ፡ የጥልቀቱ ፡ መጠን ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጉባኤና ፡ በሌሎችም ፡ ስፍራዎች ፡ ሁሉ ፡ ታይቷል ። ይኸው ፡ ጎብረትና ፡ መረዳዳት ፡ ወደፊትም ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ እየተስፋፋና ፡ እየጠነከረ ፡ እንዲሄድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ስለዚህ ፡ ክቡርነትዎ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡

ወዳጅነት ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ እርዳታና ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ እንደሚይንደልብዎ ፡ ሊተማመኑ ፡ ይችላሉ ።

ክቡር ፡ የሕንድ ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ ክቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጀዋሀርላል ፡ ኔህሩ ፡ ለላኩልን ፡ ሰላምታዎች ፡ ምስጋናችንን ፡ እንዲያቀርቡልንና ፡ በኛም ፡ በኩል ፡ ስለነርሱ ፡ ያለንን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ አክብሮትና ፡ ወዳጅነት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

472

የስዊስ ፡ ፌደራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ አንድሬይ ፡ ቧሲኤ ፡ ጥር ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፱ ፡ ሰዓት፡ በግ ፡ ልውል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፈት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የስዊስ ፡ ፌደራል ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትርና ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ አድርጎ ፡ ሲሾመኝ ፡ ለእኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብር ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በስዊስና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ የቈየው ፡ ወዳጅነትና ፡ የልብ ፡ ግምት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባደረገው ፡ የኦፊሲዬል ፡ አጐበኛኘት ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝና ፡ በበለጠ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ሊያገኝ ፡ ችሏል ።

የስዊስ ፡ ሕዝብ ፡ በየስፍራው ፡ ያደረገልዎ ፡ የድል ፡ አቀባበል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ላደረገው ፡ ጀግንነትና ፡ አድናቆት ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ነፃነትና ፡ ስለ ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ላለዎት ፡ አሳብ ፡ ምስክር ፡ ሆኗል ። በዚህም ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የስዊስ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ምኞት ፡ የተሰበረ ፡ ነው ።

በጠላት ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በጀግንነት ፡ ያደረገው ፡ ተጋድሎ ፡ ለዓለም ፡ ምሳሌነቱን ፡ ከማስረዳቱም ፡ በላይ ፡ ይች ፡ የተቀደሰች ፡ ነፃነት ፡ ልትገኝ ፡ የቻለችው ፡ በአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነፍስና ፡ በሃይማኖት ፡ ጽናት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የጋራ ፡ ተወራራሻችን ፡ ለሆነው ፡ ከሺህ ፡

ዓመት ፡ ይበልጥ ፡ ላለው ፡ የክርስቲያናዊ ፡ ታሪክ ፡ ታማኝ ፡ በመሆን ፤ አገርዎን ፡ ወደ ፡ ዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ያለዎት ፡ ጥልቅ ፡ ዘዴና ፡ የእርምጃ ፡ ወዳጅ ፡ በመሆንዎ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የስዊስን ፡ አገር ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ አንዳንዶቹን ፡ የቴክኒክ ፡ የሲአንቲፊክ ፡ የፔንሎሻክና ፡ የኩልቱሬል ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ከመመልከትዎም ፡ በላይ ፡ እንዲሁም ፡ የመድኃኒት ፡ መቀመሚያዎችንና ፡ የኢንዱስትሪኤል ፡ ቤቶች ፡ የሚሰጡትን ፡ ጥቅም ፡ በመገመገ ፡ ነት ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ተባብሮ ፡ ለመሥራት ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የጋራ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ እንዲመሠረት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የዚህን ፡ መንገድ ፡ አመልክቷል ።

ይህንንም ፡ ለማከናወን ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የሚያዋጡት ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በጠበቀና ፡ በሚገባ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለማከናወኛ ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ ምኞት ፡ ያለው ፡ የመተባበር ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ማስታወሻዎች ፡ የሚሆኑትን ፡ የዝምድና ፡ ታሪኮችን ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ለማስታወስ ፡ ያስችላቸዋል ። ከ፲፱፻ኛው ፡ ትውልድ ፡ ጀምሮ ፡ የስዊስ ፡ ሰዎችና ፡ የቋንቋ ፡ ሊቆች ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጅኦግራፊና ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ምርመራ ፡ ታውቀዋል ።

ካለፈው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አውሮፓ ፡ ውስጥ ፡ ይደነቅ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በዚች ፡ አስደናቂ ፡ በሆነችው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ የኤኮኖሚክና ፡ የጥበብ ፡ ግንኙነት ፡ ከመመሥረታቸው ፡ በፊት ፤ የተጻፉት ፡ መጻሕፍቶች ፡ ኢትዮጵያን ፡ በስዊስ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሊያሳውቋት ፡ ችለዋል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በቅርቡ ፡ በ፲፱፻ኛው ፡ ትውልድ ፡ አልፍሬድ ፡ ኢልግ ፡ የተባሉት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራዎች ፡ ለማግኘት ፡ ክብር ፡ አግኝተው ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ አንዱን ፡ ከሌላው ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ተጨማሪ ፡ ዕድል ፡ አግኝተው ፡ ነበር ። ዛሬም ፡ ወደፊት ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ለመሄድ ፡ ምኞት ፡ ያለው ፡ ትንሹ ፡ የስዊስ ፡ ኩሙዩኒቲ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በተደረገለት ፡ የልግስና ፡ መስተንግዶ ፡ ተደስቷል ። ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ሥራዎችና ፡ ተስፋዎች ፡ ለዚህ ፡ በሙሉ ፡ ሕሊና ፡ ለማከናውነው ፡ ሥራዬ ፡ እንደሚረዱኝ ፡ አምናለሁ ፤ ሥራዬን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በስዊስ ፡ ኩንፌ

ዴራሲዮን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እንዲስፋፋ ፡ ያለኝን ፡ ድካም ፡ የማላስቀር ፡ መሆኔን ፡ ስገልጽ ፡ እንዲሁም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እምነትና ፡ እርዳታ ፡ እንዲደረግልኝ ፡ መንግሥትዎንና ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስጠይቅ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝዎት ፡ መሆኑን ፡ ለመናገር ፡ እደፍራለሁ ።

ከኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ሐንሪ ፡ ቤት ፡ ደ ፡ ፊሼር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤና ፡ እንዲሁም ፡ እኔ ፡ የተሾምኩበትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ሳቀርብ ፡ ከሚሰማኝ ፡ ክብር ፡ በስተቀር ፡ እንዲሁም ፡ የፌዴራሉ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለአገሯ ፡ ስፋትና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብልጽግና ፡ እንዳሳ ፡ ርብ ፡ የታዘዝኩትን ፡ ስገልጽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የስዊስ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ስንቀበልዎ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

የስዊስ ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የተደነቀና ፡ የተወደደ ፡ መሆኑ ፡ ሊያከራው ፡ ይችላል ። በውበት ፡ ከታወቀችው ፡ አገርዎ ፡ ጋር ፡ ያለን ፡ ግንኙነት ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ በወዳጅነት ፡ መተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ በመሆኑ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በስዊስ ፡ መካከል ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጅነት ፡ ሊኖር ፡ ችሏል ።

እነዚህም ፡ የወዳጅነትና ፡ የመተሳሰብ ፡ ስሜቶች ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊመራበት ፡ በሚገባው ፡ መሠረታዊ ፡ ነገርና ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ በመሆናቸው ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ ተመሳሳይ ፡ ለመሆኑ ፡ የማይካዱ ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ። በኢትዮጵያና ፡ በስዊስ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የጋራ ፡ ጥቅምና ፡ ወዳጅነት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚያፋፋው ፡ የመሠረታዊ ፡ አሳቦችን ፡ ተመሳሳይነት ፡ በመሆኑ ፡ በንግግርዎ ፡ ውስጥ ፡ እንደገለጡት ፡ ይህ ፡ መተሳሰብ ፡ የተጀመረው ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ እንሥቶ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የወዳጅነትና ፡ የጎብረት ፡ መሠረት ፡ በየጊዜው ፡ እያ

ደገ ፡ እንዲሄድ ፡ ተስፋችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ። በመካከላችን ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ወደተዋበች ፡ አገርዎ ፡ ሄደን ፡ በዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ባደረግነው ፡ መጐብኘት ፡ ተገልጧል ።

ከእርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሚኒስትር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤና ፡ እርስዎንም ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ በደስታ ፡ ስንቀበልዎ ፡ ከፍተኛውን ፡ መልእክትዎን ፡ ለመፈጸምና ፡ በሁለቱ ፡ ወዳጅ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ መልካም ፡ መገናኛዎች ፡ ለማጠንከር ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የዘወትር ፡ እርዳታችንና ፡ መልካም ፡ አስተያየታችን ፡ የማይጓደል ልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ።

473

የቼኮስሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ጥር ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፭ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከቼኮስሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከክቡር ፡ ሙሴ ፡ አንድን ፡ ዛፕቶኒ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትርና ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ ሆኜ ፡ የተሾምኩበትን ፡ የክብር ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ለኔ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ነው ።

ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ የአገሬ ፡ መልእክተኛ ፡ እንድሆን ፡ በመመረጤ ፡ በሁለታችን ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የቆየው ፡ ግንኙነት ፡ እንዲጠበቅና ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ የኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የግል ፡ ሥራዬ ፡ ነው ። ለቼኮስሎቫኪያ ፡ እንደምሠራው ፡ ሁሉ ፤ እንዲሁም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጥቅም ፡ መስሎ ፡ የሚታየኝን ፡ ከማብ ፡ ለማድረስ ፡ ከማደርገው ፡ ድካም ፡ ከቶ ፡ ቸል ፡ አልልም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነፃነቱን ፡ ለማዳን ፡ በጀግንነትና ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ያደረገውን ፡ ተጋድሎ ፡ የቼኮስሎቫኪያ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡

ባለ ፡ ግምት ፡ ተከታትሎታል ። እንዲሁም ፡ የቼኮስሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ በበኩሉ ፡ በወራሪው ፡ ላይ ፡ መፍረድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ወራሪውን ፡ በመታገም ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ደንብ ፡ አድርጓል ።

ሥራዬን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ለሚደረግልኝ ፡ እርዳታ ፡ እምነቴን ፡ የምጥለው ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በመንግሥትዎ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ለኢትዮጵያ ፡ ብልጽግናና ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ያለኝን ፡ ምኞት ፡ በመግለጽ ፡ የተሾምኩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ እጅ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የቼኮስሎቫኪያ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ከቼኮስሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ብሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ መልካም ፡ ግንኙነት ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ የመተሳሰብ ፡ ስሜት ፡ መሆኑን ፡ አሁን ፡ ባደረጉት ፡ የተጣራ ፡ ንግግርዎ ፡ ውስጥ ፡ ገልጠውታል ።

በኢትዮጵያና ፡ በቼኮስሎቫኪያ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እያደገ ፡ መሄድ ፡ ለሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በገለጡት ፡ አስተያየት ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ በሙሉ ፡ የአሳብዎ ፡ ተካፋዮች ፡ ነን ።

ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ ግንኙነቶች ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማጠንከር ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የዘወትር ፡ እርዳታችንና ፡ መልካም ፡ አስተያየታችን ፡ እንደማይጓደልብዎና ፡ እንደዚሁም ፡ ከመንግሥታችንና ፡ ከሕዝባችን ፡ ወገን ፡ የወዳጅነት ፡ ጎብረት ፡ እንደሚያገኙ ፡ ሊተማመኑ ፡ ይችላሉ ።

ለክቡር ፡ የቼኮስሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የኛን ፡ ሰላምታዎች ፡ እንዲያደርሱልንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለቼኮስሎቫኪያ ፡ ሕዝብ ፡

ልማትና ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠ ይቅዎታለን ።

474

የመስኩብ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አሌ ክስ ፡ ፔትሮቪች ፡ የካቲት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፸፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መን ሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተና ገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የሥራ ፡ ጓደኞዬ ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤና፡ እኔ ፡ አሁን ፡ ከከፍተኛው ፡ ከሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊ ኮች ፡ ፕሬዚዲየም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥል ጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሁኜ ፡ የተሾምኩበትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊ ነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

የሶቪዬት ፡ አንድነት ፡ ሕዝቦች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያሏቸውን ፡ የሚያቋ ርጡ ፡ ስሜቶች ፡ በመልካም ፡ እንደሚጠብቋቸውና ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥ ታት ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነቶች ፡ መስፋፋት ፡ ለአገሮ ቻችን ፡ ሕዝቦች ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ እንደሚያገለግለውና ፡ እንዲሁም ፡ የሶቪዬት ፡ መንግሥት ፡ ልባዊ ፡ ምኞትና ፡ ቀዋሚ ፡ መነሻው ፡ ለሆነው ፡ ለዓለም ፡ ሰላም ፡ ማጠናከሪያን እንደሚያቀርብለት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳረጋግጥ ፡ ዕድል ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በትሕትና ፡ እየለመ ንሁ ፡ ነው ።

ከሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊኮች ፡ መንግሥት ፡ የተላ ለብኝን ፡ ተግባሮች ፡ በምፈጽምባቸው ፡ ጊዜያት ፡ ድካሞቼን ፡ ሁሉ ፡ የም መራቸው ፡ ለሁለቱም ፡ አገሮች ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ የሚያገለግሉትን ፡ የወ ዳጅነት ፡ ግንኙነቶች ፡ ለማስፋፋት ፡ በሚደረግባቸው ፡ እድገት ፡ ላይ ፡ ነው ።

ከሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊኮች ፡ መንግሥት ፡ ሙሉ፡ እምነት ፡ ተጥሎበት ፡ ለእኔ ፡ የተሰጠኝን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መልክተኛነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳውለው ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ እንዲሁም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ እርዳታና ፡ ደጋፊነት ፡ እንደማገኝ ፡ ያለኝን ፡ ተስፋ ፡ እንድገልጽ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ የማሳስበው ፡ በትሕ ትና ፡ እየለመንሁ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የዩኒዬን ፡ ሶሺ ዬት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ፕሬዚዲየም ፡ ልዩ ፡ መልክ ተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ የተሾመበትን ፡ ደብ ዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ። እንደዚሁም ፡ ከእርስዎ ፡ በፊት፡ የነበሩት ፡ የታወቁት ፡ ሚስተር ፡ ሪባኮፍ ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ስንቀ በል ፡ ሚስተር ፡ ሪባኮፍ ፡ በሁለቱ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ እየጠነከረ ፡ እንዲሄድ ፡ ያደረጉትን ፡ አገልግሎት ፡ በመልካም ፡ እናስበዋለን ።

ክቡርነትዎ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የወዳጅነት ፡ ግን ኙነት ፡ ወደፊት ፡ የበለጠ ፡ እየሰፋ ፡ እንዲሄድ ፡ በሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየትና ፡ የሚኒስትሮቻችንም ፡ እርዳታና ፡ ጎብ ረት ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ እናረጋግጥልዎታለን ። ተባብሮ ፡ በመ ሥራት ፡ ስለሚገኝ ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ ክቡርነትዎ ፡ በንግግርዎ ፡ እንደገለ ጡት ፡ ከፍተኛው ፡ መልክትዎ ፡ ይህን ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያስገኝ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

475

በመርኑቱ ፡ ምክንያት ፡ በእንግሊዝ ፡ የሙር ፡ ሠራዊት ፡ ማረፊያ ፡ በስምምነት ፡ ተሰዋቶ ፡ የነበ ረው ፡ ሪዘርብድ ፡ ኤርያ ፡ የተባለው ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መመለሱን ፡

ምክንያት ፡ በማድርግ ፡ የአጋዴን ፡ አውራጃ ፡ ባላባቶች ፡ የተሰማቸውን ፡ ደስታ ፡ ጥር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጽሑፍ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ልከው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህንኑ ፡ ደስታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ በባላባቶቹ ፡ ስም ፡ ተወክለው ፡ የመጡት ፡ ፲፪ ፡ ባላባቶች ፡ የካቲት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲገናኙ ፡ ከባላባቶቹ ፡ አንዱ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሰይድ ፡ አብዱ ፡ ከሪም ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ አጭር ፡ ቃል ።

ሀ) የአጋዴን ፡ ባላባቶች ፡ ጥር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጽሑፍ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ልከውት ፡ የነበረው ፡ ቃል ።

ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በባዕድ ፡ መንግሥት ፡ ይተዳደር ፡ የነበረው ፡ የአጋዴን ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ አገር ፡ በመጨረሻ ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ከሦርነቱ ፡ በፊት ፡ እንደነበረው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እንደሚተዳደር ፡ የሚያስረዳ ፡ መግለጫ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፯ ፲፱፻፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሬዲዮ ፡ የተነገረውን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሰምተነው ፡ ከቄየን ፡ በኋላ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ በአጋዴን ፡ ክፍል ፡ የምንገኘው ፡ ዜጎችዎ ፡ የስምምነቱን ፡ መንፈሱን ፡ ጭምር ፡ እንድንረዳ ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ድረስ ፡ መጥተን ፡ ዝርዝሩ ፡ ስለ ፡ ተነገረን ፡ ስመ፡ ጥሩ ፡ መሪነትዎ ፡ ባሰበውና ፡ ባሰናዳው ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ጥንታዊ ፡ መብቱንና ክብሩን ፡ እንዲያገኝ ፡ ስለ ፡ ተረጋገጠለት ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ቀን ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከወራሪው ፡ ወዲህ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ከሦርነቱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ተመልሶ ፡ አንድነቱን ፡ እንዳገኘ ፡ የሚቈጠርበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ያለንን ፡ ወሮታና ፡ ያላቋረጥነውን ፡ ታማኝነታችንን ፡ ለመግለጫ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡ ዕድላችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እንገልጣለን ።

ዜጎችዎ ።

* * *

ለ) የፊታውራሪ ፡ ሰይድ ፡ አብዱ ፡ ከሪም ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በድፍን ፡ አጋዴን ፡ ሕዝብ ፡ ተመርጠን ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ሥር ፡ ቆመን ፡ ሳያቋርጥ ፡ የቄየን ፡ ታማኝ ፡ ዜጎችዎ ፡ መሆናችንን ፡ ለመግለጥ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ የተላክነው ፡ ባላባቶች ፡ በተሰጠን ፡ ዕድል ፡ የተሰማንን ፡ ኩራትና ፡ ጥልቅ ፡ ደስታ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትሕትና ፡ እንገልጣለን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ አድርገን ፡ በጥር ፡ ፴ ፡ ፲፱፻፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንደራሴ ፡ የአጋዴን ፡ ባላባቶች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ሐረር ፡ ድረስ ፡ ተጠርተን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ ሪዜርቭድ ፡ ኤርያ፡ ተብሎ ፡ ሲጠራ ፡ የቄየውን ፡ የአጋዴን ፡ ሕዝብ ፡ መሬት ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ መለቀቁን ፡ ዝርዝሩን ፡ ከነትርጉሙ ፡ አስረድተው ፡ ስለ ፡ ነገሩን ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ ታላቅ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጥ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አማካይነት ፡ የተሰበሰብነው ፡ ባላባቶች ፡ በሙሉ ፡ በፊርማችን ፡ አረጋግጠን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የላክነው ፡ ጽሑፍ ፡ አስረድቶልን ፡ የቄየ ፡ መሆኑን ፡ እናምናለን ።

አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ አባታዊ ፡ በሆነው ፡ አስተያየትዎ ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆነው ፡ ዜጎችዎ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ በባዕድ ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ በቄየው ፡ መሬታችን ፡ ገብተን ፡ ተቋርጦብን ፡ የቄየውን ፡ መብታችንን ፡ ለማግኘት ፡ እንድንችል ፡ ቢደረግልንም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ልማዳዊና ፡ ሰብአዊ ፡ በሆነው ፡ ሰፊ ፡ ችሮታዎ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የሆኑትም ፡ ከዚሁ ፡ ርስታችን ፡ ከሆነው ፡ መሬታችን ፡ ላይ ፡ ለክብቶቻቸው ፡ ግርና ፡ ውሃ ፡ አግኝተው ፡ እንዲያግጡና ፡ እንዲያጠጡ ፡ ቀድሞ ፡ በዳግማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ቢደረግላቸውም ፡ ይኸንን ፡ ችሮታ ፡ ያገኙ ፡ ባለውለታ ፡ ሆነው ፡ በመገኘት ፡ ሩጎታ ፡ አቤቱታቸውን ፡ ለማሰማት ፡ ወደ ፡ ገዥዎቻቸው ፡ ሄደው ፡ ስለሚገኙና ፡ ይህ ፡ አደራረግም ፡ እኛን ፡ ሳያሳዝነን ፡ እንዳልቀረ ፡ መግለጽ ፡ የሚገባን ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየን ፡ ደግሞም ፡ ከዚህ ፡ አድራጎታቸው ፡ ጋር ፡ መንግሥታችን ፡ የጥንት ፡ ርስቱን ፡ ሲረ

ከብ ፡ ጠብ ፡ ለማጫር ፡ የሚያስቡ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ በኛም ፡ በኩል ፡ የተሰማንን ፡ ጎዘን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳንገልጽ ፡ ብናልፈው ፡ እውነተኛ ፡ ዜጎችዎ ፡ ለመሆናችን ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሆኖ ፡ እንዳይገኝብን ፡ ስላሥጋን ፡ ቀጥለን ፡ ለምናመለክተው ፡ የበቃ፡ አስተያየት ፡ እንዲጣልበት ፡ ስንል ፡ ልመናችንን ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እናቀርባለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌና ፡ ለልዑላን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ከኛ ፡ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር፡ እያልን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ምኞታችንን ፡ እናቀርባለን ።

* * *

ሐ) ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ አጭር ፡ ቃል ።

ያመለከታችሁት ፡ በሚገባ ፡ ነው ። መብታችሁም ፡ የሚጠበቅላችሁ ፡ መሆኑን ፡ እናረጋግጥላችኋለን ።

476

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ቢሾፍቱ ፡ ሐረር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተገኝተው ፡ እጩ ፡ መኰንኖቹ ፡ ያዘጋጁትን ፡ የአየር ፡ ትርአይት ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ በአየር ፡ ኃይል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ሲሰጡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

የዛሬ ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ይህንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስንመርቅ ፡ የተመኘነው ፡ እናንተ ፡ አድጋችሁ ፡ ቍጥራችሁ ፡ በርክቶ ፡ ድርጅቱም ፡ ተስፋፍቶ ፡ በትምህርት ፡ ቤትነት ፡ ተወጥኖ ፡ የነበረው ፡ ዐቅም ፡ ጐልምሶ ፡ ከለላው ፡ ከመከላከያ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ተቀላቅላችሁ ፡ የምትሠሩበትን ፡ ችሎታ ፡ አግኝታችሁ ፡ ለማየት ፡ ነበር ።

ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የተቋቋመበት ፡ ዘመን ፡ ፪ኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ጋር ፡ የተጋጠመ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ዐዋቂዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ በምንመኘው ፡ መጠን ፡ ከኤሮፓ ፡ ለማግኘት ፡ የነበረብን ፡ ችግርና ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በኢትዮጵያ፡

የአየር ፡ ኃይል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ መዋጣት ፡ አጠራጥሮ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ያገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ጊዜና ፡ ትምህርት ፡ ካገኘ ፡ ማናቸውንም ፡ ጥበብ ፡ ለመቅሠምና ፡ ለመያዝ ፡ የማያቅተው ፡ መሆኑን ፡ የተረዳነውና ፡ ያመንበት ፡ በመሆኑ ፡ ሳናመነታ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ አቋቋምን ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ተከታተልነው ፡ ከዚህ ፡ ካልተለመደው፡ ተግባር ፡ ጋር ፡ በመለማመድ ፡ ያደረጋችሁት ፡ እርምጃ ፡ የእምነታችን ፡ ማጠንከሪያ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሥራ ፡ ሕይወታችሁን ፡ የሠዉት ፡ የተቀዳሚነት ፡ ዕድል ፡ ቢያጋጥማችሁም ፡ መልካም ፡ ስም ፡ ትተው ፡ አለፉ ።

የደረሳችሁበት ፡ ደረጃና ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ፍሬ ፡ የሚያበቃው ፡ ሆኖ ፡ ስለታየን ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ተገኝተን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ለመስጠት ፡ በመቻላችን ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህም ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ስናቋቁም ፡ በሩቅ ፡ ስንመለከተው ፡ ወደነበረው ፡ ምኞት ፡ ለመድረሳችን ፡ ምልክት ፡ ሲሆነን ፡ ሌላውም ፡ ግብ ፡ እንደ ዚሁ ፡ በፋንታው ፡ እንደሚደረስበት ፡ እምነት ፡ ሰጥቶናል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲከናወን ፡ ለማየት ፡ ለረዳንና ፡ ከዚህ ፡ ላደረሰን ፡ አምላክ ፡ ምስጋናችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልንዘረዝርላችሁ ፡ አስፈላጊ ፡ አይመስለንም ። ቢሆንም ፡ ባጭሩ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ የሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያገር ፡ ነፃነት ፡ የሚታይበት ፡ የተቀደሰ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነፃነቱን ፡ ከመሠረተበት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በየጊዜው ፡ በገጠመው ፡ የችግር ፡ ማዕበል ፡ ሁሉ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ሳይታጠፍ ፡ በጐሣ ፡ ሳይለያይ ፡ በኅናናነት ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ከኛ ፡ ዘመን ፡ አድርሶታል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በንጉሡ ፡ መሪነት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ በታላቅ ፡ ቅንዓት ፡ ጠብቆ ፡ አስፈላጊውን ፡ መሥዋዕትነት ፡ በማድረግ ፡ ከዚህ ፡ እንዳደረሰው ፡ ሁሉ ፡ እናንተም ፡ ይህንኑ ፡ የቈየውን ፡ የአባቶቻችሁን ፡ መንፈስ ፡ ወርሳችሁ ፡ በማያንስ ፡ ጀግንነትና ፡ ቅንዓት ፡ እንደምትጠብቁት ፡ እናምናለን ።

ስለ ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ ጉዳይ ፡ በኛው ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡

ሁኔታ ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ የምንነግራችሁ ፡ በዛሬው ፡ ጦርነት ፡ መጠ
ነኛ ፡ የሆነ ፡ የአየር ፡ ድጋፍ ፡ የሌለው ፡ የባሕር ፡ የመሬት ፡ ጦር ፡ ሠራ
ዊት ፡ የመከላከል ፡ ተግባሩ ፡ ያየር ፡ ድጋፍ ፡ እንዳለው ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡
ሆኖ ፡ አይቃናለትም ። ስለዚህ ፡ የአየር ፡ አገልግሎት ፡ መኖር ፡ ለባሕር ፡
ለመሬት ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችን ፡ ታላቅ ፡ እርዳታ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ለምድር ፡ ኑሮአችን ፡ ማመላለሻ ፡
የሚመቸው ፡ መንገድ ፡ በተወሰነበትና ፡ መንገድም ፡ ለመሥራት ፡ ተራራ
ውና ፡ ገደሉ ፡ በረሃውና ፡ ርዝመቱ ፡ ብርቱ ፡ የገንዘብ ፡ ዐቅም ፡ በሚጠይቅ
በት ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ በተበታተነበት ፡ ሰፊ ፡ በሆ
ነው ፡ አገራችን ፡ ላይ ፡ ሕዝቡን ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ለማገናኘትና ፡ አገሪቱ
ንም ፡ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ እንድትቃረብ ፡ ለማድረግ ፡ ከጥቃትም፡ ለማ
ዳን ፡ የሚረዳው ፡ ዋናው ፡ ዘዴ ፡ በየዕለቱ ፡ እንደምታዩት ፡ ይኸው ፡ የአ
የር ፡ አገልግሎት ፡ ማስፋፋት ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ እንደየዕድላችሁ ፡ እንድትማሩ ፡ በየተማሪው ፡
ቤት ፡ የዘራናችሁ ፡ ያገራችን ፡ ልጆች ፡ ይልቁንም ፡ እናንት ፡ ካዚህ ፡ ያላ
ችሁ ፡ ወጣቶች ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ከባድ ፡ አላፊነቶች ፡ የተጣሉባችሁ ፡
ስለ ፡ ሆናችሁ ፡ የሥራችሁን ፡ ከፍተኛ ፡ ጠቃሚነት ፡ በመመልከት ፡ ዘወ
ትር ፡ ትምህርቱንና ፡ ሥራውን ፡ አሸናፊዎች ፡ እንጂ ፡ ሥራው ፡ አሸናፊ
ያችሁ ፡ እንዳይሆን ፡ በአእምሮአችሁ ፡ በትጋታችሁ ፡ ከልብ ፡ በመታዘዝ ፡
በዲሲፕሊናችሁ ፡ የበረታችሁ ፡ እንድትሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ለዚህም ፡ የሚረዳችሁ ፡ የተፈቀደው ፡ መንገድ ፡ በተገኘው፡ ዕውቀት፡
ተመክቶ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ መዝናናት ፡ ሳይሆን ፡ የጊዜውን ፡ ጥበብ ፡ በትጋት ፡
እየተከታተሉ ፡ ለማሻሻል ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ፡ መጣጣር ፡ ነው ።

ሰው ፡ በሠራው ፡ መሣሪያ ፡ መሥራት ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይደለም ።
አንዱ ፡ ወገን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ እሚሠራበትን ፡ መሣሪያ ፡ መሥራት ፡ አለ
በት ። ይህ ፡ ባይደረግ ፡ ተጠዋሪነትን ፡ መሸከም ፡ ያሳፍራል ። ማናቸውም ፡
ጥበብ ፡ እንደምናየው ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ እየተሻሻለ ፡ የሚያድር ፡
ሕይወት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሆኗል ። የታወቀውን ፡ ብቻ ፡ ዐውቆ ፡ ከዚያው ፡
ላይ ፡ ቆሞ ፡ መገኘት ፡ የሚመኙትን ፡ ዕውቀት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዐውቀ
ውት ፡ ያለፉትንም ፡ ቢሆን ፡ ሕይወት ፡ እንደሚያጣ ፡ ከማድረግ ፡ የሚያደ
ርሰው ፡ ይሆናል ።

ዓለም ፡ እምን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በየዞራችሁበት ፡ ተመልክታችሁታል።
እኛሳ ፡ ማለትን ፡ አለማሰብ ፡ አለመቅናት ፡ የነፃነት ፡ በሽታ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ በመብረር ፡ በሚካኒሲያንነት ፡ ረገድ ፡ አሁን ፡ ያገኛችሁ
ትን ፡ ኤክስፔሪያንስ ፡ በቂ ፡ በማድረግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መራመድን ፡ ያቋረ
ጣችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ የደከማችሁበትን ፡ ትምህርት ፡ ከመ
ርሳት ፡ ትደርሳላችሁ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ዘወትር ፡ ተማሪና ፡ መማሪያ ፡ እንዲ
ሆን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ወስኖበታል ።

አእምሮም ፡ ምግብ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ አትክልት ፡ ነው ። ዘወ
ትር ፡ ለምልሞ ፡ እንዲኖር ፡ ሲፈለግ ፡ ይበልጥ ፡ ለመሥራትና ፡ ይበልጥ ፡
ለማወቅ ፡ በመጣጣር ፡ የነዚህን ፡ ምግብነት ፡ ይጠይቃል ።

እስካሁን ፡ ያላጠናችሁትን ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የእስትራቴጂ ፡ ትምህ
ርት ፡ እንድታገኙ ፡ በማሰብ ፡ በስዊድን ፡ አገር ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ የአንድ ፡
ክፍል ፡ አዛዥ ፡ የሆኑትን ፡ ብርጋዴር ፡ ጀኔራል ፡ ኒልሰንን ፡ አስመጥተን
ላችኋል ።

እሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የጣልንባቸውን ፡ እምነት ፡ ፈጽመው ፡
እናንተን ፡ በትምህርታችሁ ፡ ወደታሰበው ፡ ግብ ፡ እንዲያደርሱ ፡ ተስፋ ፡
እናደርጋለን ።

ሌሎቹም ፡ አስተማሪዎቻችሁ ፡ ባደረጉት ፡ ትጋትና ፡ ጥረት ፡ ልናመ
ሰግናቸው ፡ እንወዳለን ።

477

የየጠቀላይ ፡ ግዛቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡
መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በያመቱ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ስብሰባ ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ የካቲት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭፡
ዓ ፡ ም ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ ሲሰ
ናበቱ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ) ከሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ መካከል ፡ የከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡
አስኪያጅ ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ አብ ፡ ቢያድግልኝ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕይወት ፡ ፍቱን ፡ መድኃኒት ፡ የሆነውን ፡ የትምህርት ፡ ሥራ ፡ በተሻለ ፡ አኳኋን ፡ ለማራመድና ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለማዳረስ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ በያመቱ፡ እየተሰበሰብን ፡ መመካከር ፡ ከጀመርን ፡ እነሆ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በነዚህ ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ ያደረግነውን ፡ የሥራ ፡ መሻሻል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከረጅሙ ፡ ባጭሩ ፡ በያመቱ ፡ የገለጽን፡ ቢሆን ፡ ዛሬም ፡ እንደተለመደው ፡ የ፲፱ቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ የዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የክፍል ፡ ሹማምንቶች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበን ፡ ለሥራችን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆኑት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ከተመካከርን ፡ በኋላ ፡ የጉባኤው ፡ ፍጻሜ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበናል ።

ጃ ን ሆ ይ ።

እስካሁን ፡ በ፲፱ቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ተቋቁመው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ የመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፷፫ ፡ ሲሆን ፡ በነዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ፷፯፻፱ ፯፱ ፡ ወንዶችና ፡ ፱፯፫፻፫፯፯ ፡ ልጃገረዶች ፡ ተማሪዎች ፡ በድምሩ ፡ ፩፻፫፻፻፱፯ ፡ ወጣቶች ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ በአቋቋሙዋቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙ ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፯፻፱፫ ፡ ሲሆን ፡ በጠቅላላው ፡ በ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ.ም. በአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የነበሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ፩፱፻፶፭ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

ይኸውም ፡ በቤተ ፡ ክህነትና ፡ በግል ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ሳይጨመር ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በየጊዜው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ተከታትለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ መስመር ፡ ተገኝተው ፡ አገራቸውን ፡ በማገልገል ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ በተግባረ ፡ እድ ፡ በቴክኒዮሎጂና ፡ በዩኒቬር

ስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ በእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙት ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥርም ፡ ፪፯፫፻፻፲፯ ፡ መሆኑን ፡ እየገለጽን ፡ ዛሬ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በደረጃና ፡ በክፍል ፡ መጨመር ፡ እንዲሁም ፡ በመምህራን፡ በተሻለ ፡ አኳኋን ፡ ድርጅት ፡ በማግኘታቸው ፡ ካለፈው ፡ ዓመት ፡ ይልቅ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ ሰጥተው ፡ ይገኛሉ ። ይኸውም ፡ መሻሻል ፡ የተገኘው ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አሳብ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የታዘዘው ፡ ሚኒስቴራችን ፡ የመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ በየደረጃው ፡ እንዲሰጥ ፡ አድርጎ ፡ በያመቱ ፡ ቍጥራቸው ፡ ያላነሰ ፡ መምህራን ፡ አሠልጥኖ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውሉ ፡ በመደረጉና ፡ እንዲሁም ፡ በትምህርት ፡ ቦርድ ፡ ተጠንቶ ፡ ቀርቦ ፡ የተፈቀደው ፡ የመምህራን ፡ ደመወዝ ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ በማግኘቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ መምህር ፡ በማስተማር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ስሜት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖዋል ።

ይህም ፡ አፈጻጸም ፡ እያንዳንዱን ፡ መምህር ፡ በዕውቀት ፡ እንዲጐለምስ ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ ለሥራውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትጋት ፡ አሳድሮበታል ። እንዲሁም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ መምህራን ፡ ዕውቀታቸውን ፡ በማሻሻል ፡ ለወጣቶቹ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጡ ፡ ለማድረግ ፡ በማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ በክረምቱ ፡ ወራት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለዕረፍት ፡ ሲዘጉ ፡ በቀለም ፡ ትምህርትና ፡ በማስተማር ፡ ዘዴ ፡ እንዲጐለምሱ፡ በመደረጉ ፡ ራሳቸውም ፡ ተጠቅመው ፡ ሥራውንም ፡ ጠቅመውታል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ እየጨመረ ፡ እንደ ፡ መሄዱ ፡ መጠን ፡ ለሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ የሚተላለፉት ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ በመብዛቱ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲቋቋም ፡ በፈቀደው ፡ መሠረት ፡ ድርጅቱ ፡ በተሙዋላ ፡ አኳኋን ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ በመጪው ፡ ፲፱፻፸፱ ፡ ዓ.ም. ሥራውን ፡ እንዲጀምር ፡ ታምንዋል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ይሰጥ ፡ ከነበረው ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ በቀር ፡ ሀገሪቱ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ የምትጠይቀውን ፡ አገልግሎት ፡ ለመሙላት ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይህንኑ ፡ ለማስተማር ፡ የሚችሉ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ ያላቸው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ መምህራን ፡ በየጊዜው ፡

የዚሁኑ ፡ ትምህርት ፡ ተከታትለው ፡ ስለተላኩ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎ ቹን ፡ ባዲስ ዘዴ ፡ በማሠልጠን ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

ጃ ን ሆ ይ ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በወንዶች ፡ ልጆች ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የትምህርት ፡ እርምጃ ፡ የሚያስደስት ፡ ውጤት ፡ ሲሰጥ ፡ በልጃገረዶች ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ዝቅተኛ ፡ በመሆኑ ፤ በዚህ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመ ድረስ ፡ እንዳልቻለ ፡ የታወቀ ፡ ነበር ። ለዚሁም ፡ ሴቶች ፡ ለወንዶች ፡ መተ ኪያና ፡ መከታ ፡ ለመሆን ፡ ሲችሉ ፡ በትምህርት ፡ ባለመግፋት ፡ በባል ፡ በመቀጨትና ፡ ራሳቸውንም ፡ ባለመቻል ፡ ተሰናክለው ፡ ሲቀሩ ፡ ለነሱ ፡ የወጣው ፡ ገንዘብ ፡ በከንቱ ፡ የተከሰረ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ እናት ፡ አባታ ቸውንም ፡ እንደ ፡ ወላድ ፡ መካን ፡ አድርጎ ፡ የሚያስቈጥራቸው ፡ ነው ። የሴ ቶችም ፡ ልጆች ፡ ሕይወት ፡ እንደሞተ ፡ መቈጠሩ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ግርማዊነ ትዎ ፡ የተናገረው ፡ መሪ ፡ የሆነ ፡ መሠረታዊ ፡ ቃል ፡ በልጃገረዶች ፡ ሕሊና፡ ስለተቀረጸ ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ መወዳደር ፡ ችለው ፡ በከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙት ፡ ቍጥራቸው ፡ እየጨ መረ ፡ በመሄዱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ መሆኑን ፡ ያሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እርምጃቸው ፡ ሊያስረዳ ፡ ችሏል ።

ለወደፊቱም ፡ የልጃገረዶችን ፡ የትምህርት ፡ እርምጃ ፡ በበለጠ ፡ አኳ ኋን ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማጐልመስ ፡ ደንበኛ ፡ ሴቶች ፡ መምህራን ፡ አሠል ጥኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ ስለታወቀ ፡ በመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸ ውን ፡ የሚከታተሉ ፡ ሴቶች ፡ ወጣቶች ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመ ሰለውን ፡ ተፈላጊ ፡ ትምህርት ፡ ለማስፋፋት ፡ በሰፊው ፡ የሚታሰብበት ፡ ስለሆነ ፡ በተለይ ፡ አንድ ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡ የሴቶች ፡ የመምህራን ፡ ማሠል ጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፤ ግር ማዊነትዎ ፡ በተለይ ፡ እንዲያስብበት ፡ በፍርሃት ፡ እናስታውሳለን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ የኑሮውን ፡ ደረጃ ፡ እንደማሻሻሉ ፡ መጠን ፡ ልጁም ፡ በትምህርት ፡ ሠልጥኖ ፡ እንዲገኝ ፡ በሚያደርገው፡ እሽቅድምድም፡

አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የጠያቂዎቹን ፡ ፍላ ጎት ፡ በሙሉ ፡ ለማጥገብ ፡ ባለመቻላቸው ፡ ችግር ፡ ሆኖአል ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ለሚገመተው ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በገለጽናቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ብዛት ፡ ብቻ ፡ የተወሰነው ፤ ግርማዊ ነትዎ ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ ሊደርስበት ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ወደሚጥርለት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ እታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ አዳጋች ፡ እንደሚሆን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሚሰበ ሰበው ፡ የትምህርት ፡ ግብር ፡ ገቢው ፡ እስካሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ አደርጅቶ ፡ በተጨማሪ ፡ ሊከፈቱ ፡ የሚፈለጉትን ፡ ለመጨመር ፡ ካለመቻሉ ፡ በላይ ፡ እንዲያውም ፡ ያሉትን ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለወደፊቱ ፡ ለሚያደርጉት ፡ የደረጃ ፡ እድገትም ፡ የሚ ያሳስብ ሆኖ ፡ ታይቶአል ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ ችግር ፡ ለመዳን ፡ አስፈላጊው ፡ የገንዘብ ፡ ጉልበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ መድኃኒት ፡ እንዲያገኝለት ፡ በትሕትና ፡ እን ለምናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ቃል ።

በየጊዜው ፡ እየተሰበሰባችሁ ፡ መመካከራችሁ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ነው። አሁንም ፡ በንግግራችሁ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገለጻችሁት ፡ ሁለት ፡ ጠቃሚ ፡ ማስ ታወሻዎች ፡ ልታቀርቡልን ፡ የቻላችሁት ፤ አንድነት ፡ ተሰብስባችሁ ፡ በቅ ርብ ፡ ከመመካከራችሁ ፡ የተነሣ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ አካሄድ ፡ እስካሁን ፡ ባደረጋችሁት ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ተገኝቶበታል ። ለወደፊትም ፡ ስለ ፡ ልጆቹ ፡ ትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ በሰፊው ፡ እንድታስቡበት ፡ ያስፈልጋል ። እናንተ ፡

ከዚህ ፡ እየተሰበሰባችሁ ፡ እንደምታደርጉት ፡ ሁሉ ፡ መምህራንም ፡ በቅርብ ፡ እየተገኙ ፡ ስለሚሻለው ፡ ነገር ፡ ቢነጋገሩበት ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ። በጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የአንዱ ፡ አውራጃ ፡ ከአንዱ ፡ አውራጃ፡ ተገናኝቶ ፡ የተመካከረ ፡ እንደሆን ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ በጣም ፡ እየተሻሻለና ፡ እንዲሁም ፡ ስለልጆቹ ፡ የሚታሰበው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ፡ እየተሟላና ፡ ፍሬው ፡ እያማረ ፡ ይሄዳል ።

በምትፈጽሙትም ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ለልጆቹ ፡ የምታደርጉት ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ የሚገኝበት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊዚካል ፡ የሆነውንም ፡ ነገር ፡ እንዲከታተሉ ፡ ማድረግ ፡ ዋና ፡ ጠቃሚ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በሥራም ፡ እንዲረማመዱና ፡ እንዲበረቱ ፡ በሚገባው ፡ እርዱዋቸው ። እናንተም ፡ ስትረዱዋቸው ፡ እነሱም ፡ ይረዱዋችኋል ፤ እንዲሁም ፡ ከአዳሪዎቹ ፡ በቀር ፡ ከሩቅ ፡ እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ተማሪዎች ፡ በአንዳንድ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ከትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንዳይነጠሉና ፡ እንዳይቀሩ ፡ በዘዴ ፡ ሊረዱ ፡ ይቻላል ።

ይኸውም ፡ ከሩቅ ፡ መጥተው ፡ ሲማሩ ፡ ከዋሉ ፡ በኋላ ፡ ምሳ ፡ እንዳያጡ ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜአቸው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ እየሸጡ ፡ ምግባቸውን ፡ እንዲያገኙ ፡ በማድረግ ፡ ነው ። ይህም ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ እንደነገርናችሁ ፡ ሁሉ የአምኃ ፡ ደስታ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ ችሏል ።

ለምግብ ፡ ከሚያገለግሉት ፡ አትክልቶችም ፡ በቀር ፤ ነዋሪ ፡ የሆኑና ፡ ወዲህም ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መልክ ፡ የሚሰጡ ፡ ዛፎች ፡ እንዲተከሉ ፡ እንድታደርጉና ፡ ቊጥራቸውንም ፡ እንድታስታውቁ ፡ ይሁን ። ይህም ፡ አምቦ ፡ በሚገኘው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይደረጋል ። ይህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፤ ከማንኛውም ፡ ችግር ፡ አልፈው ፡ ልጆቹ ፡ እንደየዕድላቸው ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ይችላሉ ። ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ ለሚሆነው ፡ ሕዝባችን ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለጊዜው ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ለመገኘት ፡ ባይችሉም ፡ ወደፊት ፡ በጣም ፡ እየበዙና ፡ ፍሬያቸውም ፡ እየበረከተ ፡ እንዲሄድ ፡ ዋና ፡ አሳባችን ፡ ነው ።

አሁን ፡ በንግግራችሁ ፡ ላይ ፡ እንዳስታወሳችሁት ፡ በሴቶች ፡ ልጆች ፡ በኩል ፡ የገለጻችሁት ፡ አሳብ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፤ ከልብ ፡ ተሰምቶናል ። የተደከመው ፡ ድካምና ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ መከሩ ፡ ትንሽ ፡ ነው ። ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር፡ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ የሚላኩት ፡ ሴቶች ፡ ወጣቶች ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ እየገቡ ፡ እንዲማሩ ፡ አድርገናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁላችሁም ፡ እንደምታውቁት ፡ አምና ፡ ከሐረር ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ዩኒቨርስቲ፡ ኮሌጅ ፡ ተላለፉ ። ስለዚህ ፡ የሴቶች ፡ ልጆች ፡ ቊጥር ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። እንዲህም ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ የሴቶች ፡ የትምህርት ፡ ሁኔታ ፡ ከምናስበው፡ ግብ ፡ ላይ ፡ ደርሷል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም። ስለዚህ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ አግኝተው ፡ የወንዶቹ ፡ ረዳት ፡ እንዲሆኑ ፡ በጣም ፡ እንድትተጉበትና ፡ እንድትመክሩዋቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ልናስታውሳችሁ ፡ የምንወደው ፡ በሚያስደስት ፡ አኳኋን ፡ ደኅና ፡ ደኅናውን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ጸፋችሁት ፡ ሁሉ ፡ ሌላውንም ፡ አንዳንድ ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝውን ፡ ነገር ፡ ማሳሰብና ፡ መግለጽ ፡ አለባችሁ ። ከመጥፎዎቹም ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፤ ሴትን ፡ ልጅ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሳትደርስ ፡ ከትምህርት ፡ ነጥሎ ፡ ያለ ፡ ዕድሜዋ ፡ መዳር ፡ ነው ። ትምህርትም ፡ ራሱ ፡ ቢሆን ፡ የሚጠቅመው ፡ ሕይወት ፡ ሲኖር ፡ ነው ። ሴትን ፡ ልጅ ፡ ያለ ፡ ዕድሜ ፡ መዳር ፡ እንደ ፡ መግደል ፡ ከመቆጠሩ ፡ በላይ ፡ መጫጫትና ፡ ለመጭውም ፡ ትውልድ ፡ የሚያመነምን ፡ ነው ። ይህን ፡ የመሳሰለውንም ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ።

ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄደን ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሴት ፡ ልጅን ፡ በዘጠኝና ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ መዳር ፡ እንዲቀር ፡ በማለት ፡ አዋጅ ፡ አድርገን ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ማሳየትና ፡ ማስተማር ፡ ያለባችሁ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ። የምታስተምሩትም ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጡትንና ፡ በአጠገባችሁ ፡ ያሉትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሩቁንም ፡ ሁሉ ፡ ጭምር ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

በተረፈ ፡ እስካሁን ፡ ባደረጋችሁትና ፡ በፈጸማችሁት ፡ ሥራ ፡ እናመሰግናችኋለን ።

478

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የካቲት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯፡ ዓ.ም ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ አዳራሽ ፡ ተገኝተው ፡ በንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡

ሆስፒታል ፡ የሁለተኛውን ፡ ደረጃ ፡ የነርስነት ፡ ትምህርት ፡ ለፈጸሙ ፡ ለስምንት ፡ ወጣቶች ፡ ደንበኛውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ (ዲፕሎማ) ሲሰጡ ፡ የሆስፒታሉ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ዶክተር ፡ ሆሴስ ፡ ሆል፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆስፒታል ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ አስታማሚነት ፡ ትምህርታችሁን ፡ ፈጽማችሁ ፡ የምስክር ፡ ወረቀታችሁን ፡ ስናድላችሁ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

የመጀመሪያውን ፡ እርምጃ ፡ ትምህርት ፡ በመጨረሳችሁና ፡ ይልቁንም ፡ ለሕይወታችሁ ፡ ኑሮ ፡ የመረጣችሁት ፡ ሥራ ፡ በሽተኞችን ፡ ለማስታመም ፡ ደካሞችን ፡ ለመርዳት ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ አገራችሁን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የምታገለግሉበት ፡ ስለሆነ ፡ መልካሙን ፡ መንገድ ፡ መርጣችኋል ።

አገልግሎታችሁ ፡ ትሕትናን ፡ ርኅራኄን ፡ በሥራ ፡ ጥንቁቅ ፡ ሆኖ ፡ መገኘትን ፡ ሰውነትን ፡ መማታትንና ፡ አሳብን ፡ በሙሉ ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ መጣልን ፡ ይጠይቃል ። እነዚህን ፡ መሠረታውያን ፡ ነገሮች ፡ መሪዎቻችሁ ፡ እንዲሆኑ ፡ ብታደርጉ ፡ ታላቅ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠውን ፡ ሥራችሁን ፡ ለማሳየት ፡ ትችላላችሁ ።

ክርስቲያናዊ ፡ ተግባራቸውን ፡ በመፈጸም ፡ በዚህ ፡ ሆስፒታል ፡ ሥራ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ መምህራኖቻችሁን ፡ እያመሰገንን ፡ እናንተም ፡ ለሥራ ፡ ጓደኞቻችሁ ፡ ኩራት ፡ የሆነውን ፡ ትምህርት ፡ በማጥናታችሁ ፡ ደስታችንን ፡ እንገልጽላችኋለን ።

የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱን ፡ ስም ፡ በተሸከመው ፡ ሆስፒታል፡ ላገኛችሁት ፡ ትምህርት ፡ በአኗኗራችሁና ፡ በአስታማሚነት ፡ ሥራችሁ ፡ አሁን ፡ በእጃችን ፡ ለሰጠናችሁ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተገባችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትገኙ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

479

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የካቲት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯፡ ዓ፡ም ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጐብኝተው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ እድገትና ፡ የተማሪዎቹን ፡ የትምህርት ፡ እርምጃ ፡ ሲመለከቱ ፡ ሳሉ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች።

ሀ) የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዲሬክተር ፡ የወይዘሮ ፡ ስንዱ ፡ ገብሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፤

ልዑላን ፡ መሳፍንት ፤

መኳንንትና ፡ ወይዛዝር ፤

ግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ በዓል ፡ ስለ ፡ ተገኙልን ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና፡ ወይዛዝር ፡ ጥሪውን ፡ ስላከበራችሁልን ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ስም ፡ ሁኜ ፡ በትሕትና ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ጃ ን ሆ ይ ።

ዕረፍት ፡ ከማይሰጠው ፡ አድካሚ ፡ የሥራ ፡ ጊዜው ፡ እየቆረሰ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጐበኙባቸው ፡ ሰዓቶች ፡ የመምህራን ፡ የተማሪዎችን ፡ መንፈስና ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ እያደሰ ፡ ለበለጠ ፡ ትግል ፡ የሚያዘጋጀን ፡ ረዳትና ፡ ደጋፊያችን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በዚህ ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ የምጠቅሰው ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፤ ይህን ፡ ለሴቶች ፡ ልጆች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቅጽር ፡ ቆርሰው ፡ ሕንጻውን ፡ በግል ፡ ገንዘብዎ ፡ አሠርተው ፡ በመስጠት ፡ ለአገርዎ ፡ ሴቶች ፡ አዲስ ፡ ዕድል ፡ ተልመውልናል ። ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቍጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ ሺህ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይገኙበታል ።

በ፩ኛ ፡ ደረጃ ፡ ፬፻፩ ፤

በ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ፯፻፱ ፡

ለሴቶች ፡ ባልትና ፡ መምህራን ፡ በማሠልጠኛ ፡ ክፍል ፡ ፳ ፡ ማደሪያቸው ፡ እዚህ ፡ ሆኖ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ንግድ ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ እየተመላለሱ ፡ የሚማሩ ፡ ፳፭ ፡ በድምሩ ፡ ፪፻፯ ፡ ልጆች ፡ አዳሪ ፡ ተማሪዎች ፡ የቀሩት ፡ ተመላላሾች ፡ ናቸው ።

ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ለአንድ ፡ ሺህ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚበቃ ፡ አይደለም። በ፲፱፻፸፭ ፡ ዓ.ም. አሁን ፡ ባሉት ፡ ቤቶች ፡ ፪፻፶ ፡ ተማሪዎች ፡ ይማሩበት ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለ፫፻ ፡ ተማሪዎች ፡ ብቻ ፡ ታቅዶ ፡ ሲሠራበት ፡ በቆየው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ ፭ሺህ ፡ ልጆች ፡ ይገኙበታል ።

ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የተቻለው ፡ በመንፈ ፡ ክፍል ፡ ልጆችን ፡ በማጣ በብ ፡ የዕቃ ፡ ቤትና ፡ የጸሎት ፡ ቤቱን ፡ ጭምር ፡ መማሪያ ፡ ክፍል ፡ በማድ ረግ ፡ ነው ።

ይህም ፡ ሆኖ ፡ ለሁሉም ፡ ቦታ ፡ ስላልተገኘላቸው ፡ ከ፲፯ ፡ የሚበልጡ ፡ ልጆች ፡ በድንኳንና ፡ በዛፍ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ይማራሉ ። የነዚህን ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ፍላጎት ፡ የጪት ፡ ቅዝቃዜና ፡ የቀትር ፡ ዐሐይ ፡ አልቀነሰውም። አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጤንነታቸው ፡ ስለ ፡ ታወከ ፡ ተሰናብ ተዋል ። ግርማዊነትዎ ፡ መላ ፡ ሕዝቡን ፡ ለትምህርት ፡ በጠራው ፡ መሠ ረት ፡ በያመቱ ፡ እየቀረቡ ፡ ቦታ ፡ በማጣት ፡ የምንመልሳቸው ፡ ቊጥራ ቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ በየጊዜውም ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል ።

በትምህርትና ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተጠንቶ ፡ በተሰጠው ፡ ካሪኩለም ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የትምህርት ፡ ኮርስ ፡ የ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ የሚወስድ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ዕድሜዋ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ መማር ፡ የጀመረች ፡ ልጅ ፡ ልትዘልቀው ፡ የምትችለው ፡ ፳፪ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላት ፡ ነው ። ይህ ፡ እየተዘነጋ ፡ የሴቶችን ፡ የትምህርት ፡ ፍሬ ፡ ለማየት ፡ በመጓጓት ፡ በሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ክሪቲክ ፡ ተደርጓል ። ትዳር ፡ በመያዝ ፡ ትምህርታቸውን ፡ የሚያቋርጡ ፡ እርግዥ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ይህንንም ፡ ለማቆም ፡ ታስቦ ፡ እንዲፈርሙት ፡ በተደረገው ፡ ማስገደጃ ፡ ብዙ ፡ ትግል ፡ ተፈጽሞበት ፡ በተ ገኘው ፡ ውጤት ፡ ዛሬ ፡ ሙሉ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሆኗል ።

ካሁን ፡ በኋላ ፡ የማያቋርጥ ፡ በየጊዜው ፡ ቊጥራቸው ፡ እየበረከተ ፡ የሚሄድ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃን ፡ ትምህርት ፡ የወሰዱ ፡ ልጆች ፡ ለመስጠት ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚችል ፡ ሆኗል ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የትምህርት ፡ ፈተናና ፡ ለሎንዶን ፡ ማትሪኩሌሺን ፡ ፈተና ፡ ከቀረቡት ፡ ልጆች ፡ አራቱ ፡ ፈተናውን ፡ አልፈው ፡ ሦስቱ ፡ አዲስ፡ አበባ ፡ በዩኒቬርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ይማራሉ ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ ለማትሪኩሌሺን ፡ ፈተና ፡ ዘጠኝ ፡ ልጆች ፡ ይቀመጣሉ ።

ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ እሚገኝበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ለማድ ረስ ፡ ሙሉ ፡ እርዳታ ፡ ያደረጉልንን ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ አካለ ፡ ወርቅንና ፡ በተ ለይም ፡ ሥራው ፡ በቀጥታ ፡ የሚያገናኘንን ፡ አቶ ፡ በለጠ ፡ ገብረ ፡ ጻድቅን ፡

ለማመስገን ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እለ ምናለሁ ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በነርስ ፡ በንግድና ፡ በመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ በባ ንክ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚታዩት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከመቶ ፡ ሰማኒያው ፡ የግ ርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፍሬ ፡ ናቸው ።

በትዳር ፡ ላይ ፡ የሚገኙትም ፡ በዘመናዊ ፡ ዘዴ ፡ ቤታቸውን ፡ በተሻለ ፡ ለመያዝ ፡ ልጆቻቸውን ፡ በተሻለ ፡ ለማሳደግ ፡ ስለ ፡ በቁ ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ የሴቶችን ፡ የትምህርት ፡ ግብ ፡ እንደፈጸሙ ፡ እንጂ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ከንቱ ፡ እንዳደረጉት ፡ ሊቈጠሩ ፡ አይገባም ። የአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሙሉ ፡ የሚሆነው ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ በኩል ፡ የትምህርት፡ ዕድል ፡ እንደማግኘታቸው ፡ መጠን ፡ ነው ። በየትኛውም ፡ አገር ፡ ሴቶች ፡ ከወንዶች ፡ በቊጥር ፡ ይበዛሉ ። ሴቶች ፡ የየትውልዱ ፡ እናቶች ፡ በመሆና ቸው ፡ ለወንዶች ፡ ሁሉ ፡ የመጀመሪያ ፡ መምህሮች ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የሴ ቶችን ፡ ትምህርት ፡ አስፈላጊነት ፡ መሠረታዊ ፡ ያደርገዋል ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሚናፍቀውን ፡ የትምህርት ፡ ፍሬ ፡ በቶሎ ፡ ለማየት ፡ የሴቶችን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲያበረክት ፡ የማሳስበው ፡ በትሕትና ፡ ነው ። ታሪክ ፡ ከሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ዕድል ፡ (ዴስ ቲኒ) ሴቶች ፡ የፈጸሙት ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ በታሪክ ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ገጽ ፡ ይዟል ። ሃይማኖትም ፡ ለማጥፋት ፡ ሔዋንን ፡ መጀመሪያ ፡ ሲያደርጋት ፡ ለመዳኛም ፡ እመቤታችንን ፡ ከሁሉ ፡ ቀዳሚና ፡ የመጀመሪያ ፡ ያደርጋል ።

ለኢትዮጵያ ፡ ልማት ፤
ለተማሪዎች ፡ ዕድል ፤
ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ ጤና ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ዛሬ ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስንጐበኝ ፡ ደረጃው ፡ ከፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ተሻሽሎ ፡ በማየታችን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኝቶናል ። ደስ ፡

አሰኝቶናል ፡ የምንለውም ፡ በትምህርታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አሁን ፡ በየ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ እንዳየነው ፡ ሁሉ ፡ በእጅ ፡ ሥራዎችም ፡ ጭምር ፡ ተሻሽላችሁ ፡ በመመልከታችን ፡ ነው ።

ለኑሮ ፡ ማሻሻያ ፡ ተብሎ ፡ የሚሠራውን ፡ አዲሱን ፡ የቤት ፡ አያያዝ ፡ ዐቅድ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ያሉትንና ፡ በያገሩ ፡ ሄደው ፡ እንዲያስተምሩ ፡ የተመረጡትን ፡ ወጣቶች ፡ ተሰብስበው ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጥናትና ፡ መከታተል ፡ በመመልከታችንም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በውስጡ ፡ የሚገኙት ፡ ዕቃዎች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የተ ገዙ ፡ ስለሆኑ ፡ የሀገራችን ፡ ልጆች ፡ በሚሠሩአቸው ፡ የእጅ ፡ ሥራዎች ፡ እንዲጠቀሙ ፡ ያለን ፡ መሠረታዊ ፡ ምኞቶችና ፡ አሳብ ፡ ገና ፡ ከግቡ ፡ ያል ደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ወደዚህ ፡ ምኞት ፡ መድረሻ ፡ የሆነው ፡ ዐይነተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ትም ህርት ፡ ነው ። ትምህርትን ፡ በጥብቅ ፡ መከታተል ፡ ወደዚህኛው ፡ ደረጃ ፡ ከማድረሱ ፡ በቀር ፡ ከፍ ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ የዕውቀት ፡ ደረ ጃዎች ፡ ያደርሳል ። ካንድ ፡ አገር ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ብረት ፡ ነሐስ ፡ ሌሎ ችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጠቃሚና ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የመሬት ፡ ሀብ ቶች ፡ ይወጣሉ ። እነዚህም ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ትምህርት ፡ ባስገኘው ፡ ጥበብ ፡ ሲሠሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሥራም ፡ የወንዶች ፡ ፈንታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ከፍተኛውን ፡ ትምህርት ፡ ተምራችሁ ፡ መሥራትና ፡ መከታተል ፡ አለባ ችሁ ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለሀገር ፡ ጠቃሚ ፡ ወደሆነውና ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ መጣጣርና ፡ መቅናት ፡ ያስፈልጋል ።

ከሰው ፡ አገር ፡ የመጣውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ መግ ዛት ፡ ራሴን ፡ ችያለሁ ፡ ለማለት ፡ የማያስደፍርና ፡ ግምትን ፡ ዝቅ ፡ የሚያ ደርግ ፡ ነው ። የትምህርት ፡ ቤትም ፡ ጥቅሙ ፡ ለጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ሠልጥኖ ፡ ራስን ፡ ለመቻል ፡ ጭምር ፡ ነው ። ሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ዛሬ ፡ የደረሱበትን ፡ ደረጃ ፡ በራዲዮ ፡ ሰምቶና ፡ ጽሑፎ ችን ፡ አንብቦ ፡ እነዚህ ፡ ከደረሱበት ፡ ለመድረስ ፡ በጋለ ፡ ቅንዓት ፡ በር ትቶ ፡ መነሣትና ፡ መሥራት ፡ ያስፈልጋል ።

ሙሉ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚባለውም ፡ ሴቶች ፡ በሚገባ ፡ ተምረው ፡ ከወ ንዶች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በመተባበር ፡ ሲሠሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የወንዶች ፡

ልጆች ፡ ብቻ ፡ በትምህርት ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ሙሉ ፡ ሊያደርገው ፡ አይች ልም ። ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ እንደተባለው ፡ ሁሉ ፡ ተምራችሁ ፡ ከወንዶቹ ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆናችሁ ፡ ሀገራችሁን ፡ የሚያኮራ ፡ ሥራ ፡ ለመሥ ራት ፡ የሚያስችለውን ፡ ትምህርት ፡ ጠንክራችሁ ፡ ስትማሩ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። በማናቸውም ፡ ሠለጠኑ ፡ በሚባሉት ፡ አገሮች ፡ የሚታዩት ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ከትምህርት ፡ በተገኙ ፡ ዕው ቀቶች ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ።

በኢትዮጵያ ፡ ሴቶቹና ፡ ወንዶቹ ፡ ወጣቶች ፡ የቀረበላችሁን ፡ ሰፊ ፡ የትምህርት ፡ ገበታ ፡ በመሳተፍ ፡ አእምሮአችሁን ፡ ማጐልመስና ፡ ስለሀ ገራችሁ ፡ ታላቅነት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትጋት ፡ መሥራት ፡ አለባችሁ ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በጥብቅ ፡ ከሠራና ፡ ስለ ፡ እድገቱ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ በንቃት ፡ ከተከታተለ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመድረስ ፡ ምንም ፡ የሚያ ዳግተው ፡ ነገር ፡ የለም ።

ሀገራችን ፡ ሀብታም ፡ ናት ፤ የሚጐድላት ፡ ነገር ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ የምትጠባበቀው ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ እናንተ ፡ በዘመናዊ ፡ ዕውቀት ፡ ጐልምሳችሁ ፡ ላገልግሎት ፡ እንድትደርሱላት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ትምህርታ ችሁን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ከማድረሳችሁ ፡ በፊት ፡ ለማቋረጥ ፡ በ መፈለግ ፡ ምክንያት ፡ አታብዙበት ። ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ልዩ ፡ ልዩዎ ቹን ፡ ክፍሎች ፡ ስንጐበኝ ፡ በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የተመለከትነው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ የሕፃናትን ፡ መልካም ፡ አስተዳደግና ፡ አያያዝ ፡ ጭምር ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ዕድለኞች ፡ ሁናችሁ ፡ እዚህ ፡ እተሻሻለው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ደር ሳችሁ ፡ በተሻሻለው ፡ አስተዳደግና ፡ አያያዝ ፡ ለመጠቀም ፡ ቻላችሁ ፡ እ ንጂ ፡ ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ ለሕፃናት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዕድል ፡ አልነበራች ውም ። በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ያላደገ ፡ ሕፃን ፡ ሕዋሳቶቹ ፡ ካለመጐ ልመሳቸው ፡ በላይ ፡ ጥንካሬ ፡ የሌላቸው ፡ ይሆናሉ ።

ስለዚህ ፡ እናንት ፡ ከዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የምትማሩ ፡ ወጣቶች ፡ ከቀረው ፡ ትምህርታችሁ ፡ ጋር ፡ ይህ ፡ የምትማሩት ፡ የሕፃናት ፡ አስተዳ ደግ ፡ ትምህርት ፡ ጥቅሙ ፡ ለራሳችሁ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነው ።